# ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል
## 9 ኛ ሳምንት
## ዮሴፍ የእስረኞችን ሕልም ተረጐመ

## 9ኛ ሳምንት

### ዓለማ

❖ ስለ ዮሴፍና እና ከእግዚአብሔር ስለተሠጠው ጸጋ በቀጣይነት መማር፣

### ምንባባት

❖ ዘፍጥረት 40 እና 41

### መግቢያ

❖ ባለፈው ትምህርት ዮሴፍ ለምን እስር ቤት እንደተጣለ ተምረናል፡፡ ዛሬም ከዮሴፍ ጋር የነበሩ ሁለት ሰዎች ያዩትን ሕልም እንማራለን፡፡ ዮሴፍ ሕልሙን እንዴት እንደፈታላቸውና ለሁለቱ እስረኞች እንደሕልማቸው የተፈፀመላቸውንም እናያለን፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. ዮሴፍ ወደ ግብፅ ከተወሰደ በኂላ  ምን ሆነ?
2. ዮሴፍ ስላደረገው እግዚአብሔር ባረከው? ለምን?

### ትምህርቱ

❖ ዮሴፍ በግብፅ እስር ቤት እያለ፣ የፈርኦን ጠጅ አሳላፊ እና እንጀራ  አብዛ(ዳቦ ጋጋሪ) ፈርኦን ጥፋት ሠርተው ታሠሩ፡፡ ፈርኦን ማን እንደሆነ ታስታውሳላችሁ? የግብፃውያን ንጉሥ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ዮሴፍ ሁለቱን (ጠጅ አሳላፊንና እንጀራ ጋጋሪውን) ፊታቸው አዝኖ ተመለከታቸው፣ ችግሩን ሲጠይቃቸውም እያንዳንዳቸው ሕልም እንዳዩና ትርጉሙን እንዳልተረዱት ነገሩት፡፡ ዮሴፍ ሕልሙን ይተረጉምላቸው ጀመር፡፡

❖ የጠጅ አሳላፊው «ሦስት ሃረግ ያለበትን የወይን ዛፍ በፊቴ አየሁ÷ ቅጠልና አበባ አወጣች÷ ዘለላም አንጠለጠለች÷ የዘለላዋም ፍሬ በሰለ፤ የፈርኦንም ጽዋ በእጄ ነበር፤ ፍሬውንም ወስጄ በፈርኦን ጽዋ ጨመቅሁት÷ ጽዋውንም ለፈርኦን በእጄ ሰጠሁት፡፡» ብሎ ሕልሙን ነገረው፣ ዮሴፍም «ሦስቱ ሃረግ ሦስት ቀን ነው በሦስት ቀን ፈርኦን ወደሹመት ይመልስሃል፡፡እንደቀድሞው ሥርዓትም የፈርኦንን ጽዋ በእጁ  ትሠጣለህ፡፡» ብሎ ከተረጐመለት በኂላ የኔንም ነገር ለፈረኦን ነግረህ ከእስር አስፈታኝ አለው፡፡

❖ ዳቦ ጋጋሪውም ይህን ሰምቶ ሕልሙን ለዮሴፍ እንዲህ ሲል ነገረው፡፡ «ሦስት ነጭ መሶብ እንጀራ በራሴ ላይ ነበር፡፡ በላይኛውም ፈርኦን ከሚበላበት ጋጋሪዎች ሥራ ነበረበት ወፎቹም ከመሶቡ ይበሉ ነበር፡፡»»

❖ ዮሴፍም ከሦስት ቀን በኂላ ፈርኦን እንደሚገድለውና ወፎች ሥጋውን እንደሚበሉት ተረጐመለት፡፡

❖ ከሦስት ቀናት በኂላም ዮሴፍ እንደተረጐመው ተፈጸመ፡፡ ጠጅ አሳላፊው ግን ዮሴፍ የነገረውን ዘነጋው፡፡

**ይቆየን፡፡**